# የደም ነዋይ



# Blood Money

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ድንበር ተሻጋሪ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ
አዘዋዋሪዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ያካሄደውን ኦፕሬሽን መነሻ ያደረገ እውነተኛ ታሪክ

© ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት
ሰኔ 2012 ዓ.ም

በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ውስጥ ብቻ የሚሰራጭ

# የደም ነዋይ

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ድንበር ተሻጋሪ ህገ ወጥ
የጦር መሣሪያ አዘዋዋሪዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ
ያካሄደውን ኦፕሬሽን መነሻ ያደረገ እውነተኛ ታሪክ

# Blood Money

በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት
የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ
ስልክ:- 0115 58 45 37

# ማውጫ ገጽ


የዳይሬክተር ጀነራል መልዕክት ........ 3

እንደ መነሻ ........ 4

የጽሁፉ ዓላማ ........ 5

የጽሁፉ ተደራሽነት ........ 5

የጽሁፉ ግብዓቶች........ 5

የደም ነዋይ ........ 6

- ሲጀመር ........ 6
- ‹‹መረጃ አይናቅም ፤ መረጃ አይደነቅም››........ 8
- ኮንቴይነሮቹን በእጅ የማስገባት ትንቅንቅ ........ 9
- የተቆለፈው ምስጢር ሲገለጽ........ 12
- ብስለት የወለደው ውሳኔ ........ 14
- የመጨረሻው መጀመሪያ ፤ የመጨረሻው መጨረሻ ........ 18
- እነማን በቁጥጥር ስር ዋሉ ? ........ 24
- ከጦር መሣሪያ ዝውውሩ ጀርባ ያደፈጠው ድብቅ አላማ ........ 25
- ህጉ ምን ይላል ? ........ 26
- እንደ ማጠቃለያ........ 26

ግብረ መልስ ........ 27



**ኮሚሽነር ደመላሽ ገብረሚካኤል**

*የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል*


ለአገራዊ ደህንነት ስጋት የሚሆኑ ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ መምጣታቸው ግልጽ ነው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ የምትገኝበት የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና አጋላጭ ሁኔታዎችን ከፍ የሚያደርጉ ነባራዊ እውነታዎች ይንጸባረቁበታል፡፡ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የሌላቸው አገራት መገኘት፣ ሽብርተኝነት፣ የእርስ በርስ ግጭት፣ የተለያዩ ድንበር ዘለል ወንጀሎችና ህገወጥ ድርጊቶችም መበርከታቸው በዚህ ቀጣና አገራዊ ደህንነትን አስጠብቆ ለመዝለቅ ስጋትን ከሩቅ ለይተው የሚያዩ የንስር ዓይኖችና ለማስቀረትም ሳይታክቱ የሚተጉ በብልሃት የተካኑ የመረጃና ደህንነት አመራሮችና ባለሙያዎች እንደሚያስፈልጉ ያመላክታል፡፡

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከቱርክ በጅቡቲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ በነበረ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ላይ ከመነሻው ጀምሮ ያካሄደው ክትትልና ያከናወነው ኦፕሬሽን የዚህ መገለጫ ነው፡፡ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የተቋሙ አመራሮችና ባለሙያዎች በተሳተፉበት ኦፕሬሽን በአገራዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችል የነበረ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ በቁጥጥር ስር ሊውል ችሏል፡፡

ይህ ኦፕሬሽን መረጃ ሳይናቅ እስከ መጨረሻው ክትትል ከተደረገበት በርካታ ማስረጃዎች ከኋላ እየተከተሉ አገርን የሚታደግ ስራ ማከናወን እንደሚቻል የተማርንበት ነው፡፡ ብልሃት፣ ቆራጥነት፣ አስተዋይነት፣ ትጋት፣ ከችግር መውጫ ዘዴዎችን የማፍለቅ ብቃት፣ ምስጢር ጠባቂነት ተባብረው ተቋማዊ ተልዕኮን ማሳካት እንደሚቻል ትምህርት የተቀሰመበትም ጭምር፡፡

ከመነሻው እስከ መጨረሻው የታለፈውን ውጣውረድ፣ የተገኘውንም አገርን ከጥፋት የሚታደግ ስኬት በዚህ መልኩ ለህትመት ማብቃቱ ተሞክሮ ይቀሰምበታል፣ ለተሻለ ስኬትም ያነሳሳል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በሂደቱ ለተሳተፉት በሙሉ አድናቆትና ምስጋናን እያቀረብኩ፣ ለበለጠ ውጤት እንትጋ እላለሁ !!!

# እንደ መነሻ



ምስራቅ አፍሪካ በተለይም ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ ለዓመታት በዘለቀ ጦርነት፣ የእርስ በርስ ግጭት፣ ሽብርተኝነት እንዲሁም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል የሚፈተን አካባቢ ነው፡፡ ቀውሶቹ ውስጣዊ መነሻ ቢኖራቸውም፤ የሌሎች አካላት ጣልቃ ገብነት አስተዋጽኦ ቀላል እንዳልሆነ በማስረጃ ተደግፎ ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡ በተለይ ችግሮችን በማባባስና በማወሳሰብ የሚጠቀሰው ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ ለአዘዋዋሪዎቹ ከፍተኛ ገንዘብ ሲያስገኝ፤ ለበርካታ ንጹኃን ሰዎች ግን የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የመፈናቀልና የሰቆቃ ምክንያት መሆኑን ዛሬም ቀጥሏል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሪፖርት እንደሚያመለክተው በመላው ዓለም አንድ ቢልዮን አነስተኛ የጦር መሣሪያዎች ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ተሰራጭተዋል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ አዘዋዋሪዎችም በዚህ ህገ ወጥ ንግድ በአመት እስከ አንድ ቢልዮን ዶላር ረብጣ ወደ ኪሳቸው ያስገባሉ፡፡ የ 500 ሺ ሰዎች ህይወትም ይቀጠፋል፡፡ በምስራቅ አፍሪካም 7 ነጥብ 8 ሚልዮን አነስተኛ ህገ ወጥ መሣሪያዎች ህጋዊ ፈቃድ በሌላቸው ሰዎች የተያዙ ሲሆን፤ በርካቶችም ህይወታቸውንና አካላቸውን እንደሚያጡ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

ኢትዮጵያም የቀጣናው አንድ አካል በመሆኗ የችግሩን ገፈት ከመጋራት ባለፈ የብሔራዊ ደህንነት ስጋትም እየሆነባት ይገኛል፡፡ በተለያየ መንገድና አቅጣጫ የሚገባው ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ የዜጎች ህይወት እንደዋዛ እንዲቀጠፍ ምክንያት እየሆነ ነው፡፡ በመሣሪያ የታገዙ ዘረፋዎች እንዲስፋፉም አድርጓል፡፡ ማንነትንና ሃይማኖትን ምክንያት አድርገው የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በህገ ወጥ መንገድ በገቡ መሣሪያዎች ታግዘው የቀውስ ምንጭ ሲሆኑ ተስተውሏል:: በህገ ወጥ መንገድ የሚገቡትና የሚሰራጩት የጦር መሣሪያዎች የፖለቲካ አላማን በሃይል ለማስፈጸም የሚውሉ ግብአቶችም ሆነዋል፡፡

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በተከታታይ ባደረጋቸው ክትትሎችና ኦፐሬሽኖች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ህገ ወጥ የጦር መሣሪያዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ አድርጓል:: በቅርቡም በዚህ የደም ነዋይ ተደራጅተውና ተሳስረው ከአገር ውጪና በአገር ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖችና ግለሰቦችን ህገ ወጥ መረብ በመከታተል ኢትዮጵያን ከተደገሰላት የጥፋት ሴራ የሚታደግ ኦፐሬሽን አካሂዷል:: የኦፐሬሽኑን ሂደትና ፍጻሜ በተመለከተ ሙሉ ምስሉን የሚያሳየው ታሪክ በዚህ ጽሁፍ ቀርቧል፡፡





## የጽሁፉ ዓላማ

የዚህ ጽሁፍ አላማ የመረጃ ስምሪት ኪነሙያን በጥብቅ ዲሲፕሊን በመከተል የተደራጁ ድንበር ተሻጋሪ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ አዘዋዋሪዎችን መቆጣጠር ከተቻለበት ኦፕሬሽን የሚገኘውን ተሞክሮ ለሁሉም የአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ማጋራት ነው፡፡

## የጽሁፉ ተደራሽነት

በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን በተመለከተ የተካሄደውን ኦፕሬሽን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀው ጽሁፍ ለተቋሙ የተለያዩ ዋና መምሪያዎች እንዲሁም ተገቢ ተብለው ለታመነባቸው ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ይሆናል፡፡ በተለይም በብሔራዊ የመረጃ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ለስልጠና ግብዓትነት ይውላል፡፡

## የጽሁፉ ግብዓቶች

ይህን ጽሁፍ ለማዘጋጀት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አመራሮች የሰጡት ግብዓት፤ የተሰራውን ኦፕሬሽን አስመልክቶ በአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተጠናቀሩ መረጃዎች፤ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አማካኝነት በየካቲት ወር የተዘጋጀው ‹‹ከቱርክ በጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ በገባ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ የጦር መሣሪያ እና አዘዋዋሪዎች ላይ የተከናወነ ኦፕሬሽን ሪፖርት›› የሚል ሰነድ እንዲሁም በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት፣ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን፣ በዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት፣ በአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ (አዲስ ቲቪ) ፣ በኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (ኦ ቢ ኤን) እና በአማራ መገናኛ ብዙሃን በተመሳሳይ ሰዓት መጋቢት 3 ቀን 2012 ዓ.ም የተላለፈው ‹‹የደም ነዋይ›› የተሰኘው ዶክመንተሪ ፊልም በግብዓትነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

# የደም ነዋይ


## ሲጀመር

ሰኔ 12 ቀን 2011 ዓ.ም በርካታ ኮንቴይነሮችን የጫነች መርከብ ከቱርክ ሜሪሲን ወደብ ተነስታ መዳረሻዋን ጅቡቲ ወደብ አድርጋ ጉዞ ጀመረች፡፡ መርከቧ ከያዘቻቸው ኮንቴይነሮች መካከል ሁለቱ ባለቤትነታቸው በሊቢያ ዋና ከተማ ትሪፖሊ በሚገኘው አልዛድ የቤት እቃ አስመጪ ድርጅት የተመዘገቡ ሲሆን፤ ሊበርቲ ሺፒንግ ኤንድ ሎጀስቲክስ (liberty shipping & logistic LLC) በተባለ መቀመጫውን አሜሪካ ባደረገ ድርጅት አማካኝነትም እንደተጫኑና እንደሚጓጓዙ የሰነድ ማስረጃዎች አመልክተዋል፡፡

መርከቧ በጅቡቲ መልህቋን ጥላ ኮንቴይነሮቹን ካራገፈች በኋላ፤ የሁለቱ ኮንቴይነሮች የመጨረሻ መዳረሻ አገርና ተቀባያቸውም ማን እንደሆነ ሳይታወቅ እስከ ህዳር አጋማሽ በወደቡ መጋዘን ውስጥ ከርመዋል፡፡

Liberty Shipping & Logiste LLC.

AL-Zad Co. For Import Home Furnitures & Office Furnitures &Supplies , hand tools
8 Merzan St. Al-wehdah Bldg. Tripoli - Libya





# ‹‹መረጃ አይናቅም፤ መረጃ አይደነቅም››

በሁለቱ ኮንቴነይሮች ውስጥ ምን እንዳለ የሚያውቁት ሰዎች መዳረሻው ኢትዮጵያ እንዲሆን ወስነው ያጓጓዙት ሲሆን፤ ወደዚህች አገር የሚገባበትን መላ ሲያበጃጁ ከርመው በአንድ የትራንዚት ኩባንያ ውስጥ ከሚሰራ የጅቡቲ ዜግነት ካለው ሰው ጋር ምክር ያዙ፡፡ ‹‹ወደብ ላይ ያሉትን ሁለት ኮንቴይነሮች ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ የሚያሻግርልን እና የሚረከበን ህጋዊ አስመጪ ድርጅት ብናገኝ የመጋዘን ኪራይ፣ ማጓጓዣ እና ሌላውንም ወጪ እራሳችን እንሸፍናለን›› የሚለው ያልተለመደ ማግባቢያቸው ግን ጥርጣሬ የሚያጭር ነበር፡፡ ግለሰቡ የሆዱን በሆዱ ይዞ ጥቆማውን ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ያቀብላል፡፡

**ህዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም** ኮሚሽኑ የደረሰውን ጥቆማ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አስተላለፈ፡፡ ‹‹መረጃ አይናቅም፤ መረጃ አይደነቅም›› የሚለውን አባባል መነሻ ያደረጉት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል፣ ምክትላቸው እና የአንድ ዋና መምሪያ ምክትል ዳይሬክተር ጠቋሚው የጅቡቲ ዜጋ ሙሉ ወጪው ተሸፍኖ በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ አደረጉ፡፡ ጥቆማ ሰጭውም በዕለቱ አዲስ አበባ ገብቶ ሁለቱን ኮንቴይነሮች ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት እየተደረገ ያለውን ጥረትና የኮንቴይነሮቹን ላኪዎች የተመለከተውን መረጃ አጋራቸው፡፡

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኃላፊዎች ከጥቆማው ተነስተው ጉዳዩን ሲያጤኑት አንዳች የሚያጠራጥር ነገር አገኙበት፡፡ በተለመደው አሰራር ከውጭ አገር እቃ የሚያስገባ አስመጪ ከወደብ ኪራይ እስከ ማጓጓዣ ወጪውን እራሱ የሚሸፍን ሆኖ ሳለ፤ አሁን ላኪው ‹‹ወጪውን እራሴ እሸፍናለሁ›› ማለቱ ነበር አንዳች ድብቅ ነገር ቢኖር ነው የሚል ጥርጣሬ ያጫረባቸው፡፡ ኮንቴይነሮቹ በውስጣቸው ምን ይዘዋል ? ለምን አላማስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ተፈለገ? ከማን ወደ ማን ፣ ለምን እና እንዴት ተላኩ ? ጥቆማው ወደ ጥርጣሬ፤ ጥርጣሬው ወደ እርምጃ አመራ …

> ኮንቴይነሮቹ በውስጣቸው ምን ይዘዋል ? ለምን አላማስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ተፈለገ? ከማን ወደ ማን ፣ ለምን እና እንዴት ተላኩ ? ጥቆማው ወደ ጥርጣሬ፤ ጥርጣሬው ወደ እርምጃ አመራ …

# ኮንቴይነሮቹን በእጅ የማስገባት ትንቅንቅ

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኮንቴይነሮቹን በእጁ ለማስገባት አማራጭ የሌለውን በጠንካራ ሽፋን ላይ የተመሰረተ አንድ መንገድ መከተል ነበረበት:: ፈታኝ ቢሆንም ውጤት እንደሚኖረው በማመን ተቋሙ የፈጠረውና የሚቆጣጠረው አስመጪ ድርጅት በማቋቋም ከላኪዎቹ ጋር ተደራድሮና አሳምኖ ኮንቴይነሮቹን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያስገባ የሚል መላ እንደመፍትሄ ቀረበ::

የኮንቴይነሮቹ ላኪዎች ህጋዊ የአስመጪነት ፍቃድ ያለውና ሌሎችንም የአገሪቱን መስፈርቶች የሚያሟላ ድርጅት እያፈላለጉ ስለነበር፣ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አማካኝነት ህጋዊ መስፈርቶች ተጠብቀው ለሽፋን የሚያገለግል አንድ የአስመጪ ድርጅት ተቋቋመ:: በድርጅቱ ውስጥም የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አንድ አባል ለመመሳሰል የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ባሟላ መንገድ የደንበኞች እና ሎጀስቲክስ ኃላፊ በሚል ተመደበ:: የዚህ አስመጪ ድርጅትና የአባሉ ዋና ተልዕኮም ሁለቱን ኮንቴይነሮች ከላኪው ድርጅት ጋር ተስማምቶ እና ተደራድሮ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ነው::

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል፣ ምክትላቸው እና የአንድ ዋና መምሪያ ምክትል ዳይሬክተር የደረሳቸውን መረጃ ካብላሉ፣ ከተነተኑ እና በጥልቀት ከፈተሹ በኋላ ኮንቴይነሮቹ ከዛች ቅጽበት ጀምሮ በክትትል ስር መሆን እንዳለባቸው፤ ጉዳዩም በሶስቱ አመራሮች ብቻ በምስጢር እንዲያዝ ወሰኑ፤ የተደራጀ የኦፕሬሽን ዕቅድም ነደፉ::

> የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል፣ ምክትላቸው እና የአንድ ዋና መምሪያ ምክትል ዳይሬክተር የደረሳቸውን መረጃ ካብላሉ፣ ከተነተኑ እና በጥልቀት ከፈተሹ በኋላ ኮንቴይነሮቹ ከዛች ቅጽበት ጀምሮ በክትትል ስር መሆን እንዳለባቸው፤ ጉዳዩም በሶስቱ አመራሮች ብቻ በምስጢር እንዲያዝ ወሰኑ፤ የተደራጀ የኦፕሬሽን ዕቅድም ነደፉ::

በጅቡቲ ዱራሌ ኮንቴይነር ተርሚናል የሚገኙትንና በተመረጠ አስመጪ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የተፈለጉትን ኮንቴይነሮች ክትትል በማድረግ በውስጣቸው የተደበቀውን ምስጢር ማወቅ እና በእጃቸው ማስገባት የኦፕሬሽኑ ግብ ነበር::

ነገሮች በታቀዱት መሰረት መጓዝ ጀመሩ፡፡ ከቱርክ ተነስተው ጅቡቲ የደረሱት ሁለት ኮንቴይነሮች ላኪ ሊበርቲ ሺፒንግ ኤንድ ሎጀስቲክስ ንብረቶቹን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ፍቃደኝነቱን ከገለጸው በሽፋን ከተቋቋመው አስመጪ ድርጅት ጋር የኢሜይል ልውውጥ አደረገ፡፡ የተቋቋመው አስመጪ ድርጅት ኮንቴይነሮቹን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ሂደት ሊሟሉ ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል በኮንቴይነሮቹ ላይ ባዶ ሆኖ የተቀመጠው የመዳረሻ አገር አድራሻ እንዲሞላ እንዲሁም በውስጡ ያሉትን የቁሳቁስ አይነትና መጠን የሚያሳየው ህጋዊ ሰነድ ወይም ኮሜርሺያል ኢንቮይስ (commercial invoice) እንዲደርሰው ጠየቀ፡፡

ላኪው ሊበርቲ ሺፒንግ ኤንድ ሎጀስቲክስ ኮንቴይነሮቹን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ተስማምቶ ሂደቱን ለመጀመር ለአስመጪው ድርጅት ጥያቄ ግማሽ መልስ ሰጠ፡፡ የሁለቱን ኮንቴይነሮች የመዳረሻ ስፍራና የእቃዎች መዘርዝር ቢጠየቅም የላከው ግን የአንዱን ኮንቴይነር ብቻ ነበር፡፡ ላኪው ድርጅት ይህን ያደረገው አንዱ ኮንቴይነር ለሙከራ ይግባና ሁለተኛው ይከተላል ከሚል ጥርጣሬ የፈጠረው ውሳኔ መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡ የመዳረሻ አገር አድራሻ እንዲሞላ እንዲሁም በኮንቴይነሩ ውስጥ ያሉትን የቁሳቁስ አይነትና መጠን የሚያሳየው ኮሜርሺያል ኢንቮይስ እንዲደርሰው ከፍተኛ የማሳመን ስራ የሰራው አስመጭው ድርጅት መስመር የያዘው ነገር ከእጅ እንዳያፈተልክ አንዱን ኮንቴይነር አስቀድሞ ሁለተኛውንም አስከትሎ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ተስማማ፡፡

**ጥር 4 ቀን 2012 ዓ.ም** ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኮንቴይነሮቹን በሽፋን በፈጠረው አስመጪ ድርጅት በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የመደበው የአስመጪው ድርጅት የደንበኞች እና ሎጀስቲክስ ኃላፊ ወደ ጅቡቲ አቀና፡፡ የአንድ አስመጪ ድርጅት ሰራተኛ በሚል ሽፋን ጅቡቲ የገባው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኦፊሰር ኮንቴይነሩን ጭኖ ለመውጣት አስፈላጊውን ሁሉ ሰነድ አሟላ፡፡ ክፍት የነበረው መዳረሻ አገር ከላኪው ሊበርቲ ሺፒንግ ኤንድ ሎጀስቲክስ ጋር በመነጋገር ኢትዮጵያ ተብሎ ተሞላ፡፡ ቢል ኦፍ ሎዲንግ (bill of loading)፣ፓኪንግ ሊስት (packing list) እና ኮሜርሺያል ኢንቮይስ (commercial invoice) የመሳሰሉ አስፈላጊ መረጃዎችንም ከላኪው ድርጅት ተቀበለ፡፡ አሁን ከሁለቱ አንዱን ኮንቴይነር ከጅቡቲ ለማንሳት እና ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ አስፈላጊው መስፈርት ሁሉ ተሟልቷል፡፡

ከሁለቱ ኮንቴይነሮች አንዱን ወደ ኢትዮጵያ የማስገባቱ ሂደት ተጠናቀቀ ሲባል፤ እቃው ከጅቡቲ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን በኩል የውጭ ምንዛሪ

> የውጭ ምንዛሪ መግለጫ ደብዳቤው ካልተገኘ ተልዕኮው ይከሽፋል፤ በውስጡ ምን እንደያዘ ያልታወቀው ኮንቴይነርም ከአገሪቱ የመረጃና ደህንነት ተቋም እጅ ይወጣል:: በማን እጅ ሊገባ እንደሚችልም አይታወቅም

መግለጫ ደብዳቤ (letter of credit) ተጠየቀ:: ይህ ደብዳቤ ከሌለ ኮንቴይነሩ የኢትዮጵያን ጉምሩክ ኬላዎች ማለፍ አይችልም:: በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ለሽፋን የተከፈተ አስመጪ ድርጅት መሆኑ ተገልጦ ኮንቴይነሩ እንዳያልፍ ሚስጢሩ ይበተናል:: ደብዳቤውን ማፃፍም በተመሳሳይ መንገድ ለዘመቻው ምስጢር መባከን ምክንያት ሊሆን ይችላል:: በዚህ የተነሳም ሁለተኛው ኮንቴይነር ከእጅ ይወጣል::

የሁለተኛው ኮንቴይነር እጣ ፋንታም የመጀመሪያውን ኮንቴይነር ወደ አትዮጵያ በማስገባት ስኬትና ውድቀት ላይ ስለሚመሰረት ቀጣይ ሂደቶችን በጥንቃቄ መምራት ያስፈልጋል:: በዚህም የተነሳ ጉዳዩ ኦፐሬሽኑን እየመሩ ላሉት የተቋሙ ዳይሬክተር ጀነራል እና ምክትላቸው ሊያልፉት የሚገባ ትልቅ ፈተና ሆነ::

ላኪዎቹ የአንዱን ኮንቴይነር አስፈላጊ መረጃ ካሟሉ በኋላ ሁሉንም የፍተሻ ኬላዎች አልፎ የመጨረሻ መዳረሻው ላይ የሚገባበትን ቀን እየተጠባበቁ ነው:: ኮንቴይነሩ ምን እንደያዘ ስለሚያውቁ መጨረሻውን ለማየት እንቅልፍ አጥተዋል:: የመጀመሪያው ኮንቴይነር ወደ ኢትዮጵያ መግባት ለሁለተኛው ከንቴይነር ብቻ ሳይሆን፤ ወደፊትም ወደ አገሪቱ መላክ ያሰቧቸውን ኮንቴይነሮች እጣፋንታም ስለሚወስን ሂደቱን በጣታቸው ቆመው ይከታተላሉ::

በአንድ በኩል ከላኪዎቹ ግፊት በርትቷል፤ ወዲህ ደግሞ የአገር ደህንነትን ከመጠበቅ አንጻር አስቸኳይ ውጤት ይጠበቃል፤ ሁኔታውም አጣብቂኝ ፈጥሯል::የውጭ ምንዛሪ መግለጫ ደብዳቤው ካልተገኘ ተልዕኮው ይከሽፋል፤ በውስጡ ምን እንደያዘ ያልታወቀው ኮንቴይነርም ከአገሪቱ የመረጃና ደህንነት ተቋም እጅ ይወጣል:: በማን እጅ ሊገባ እንደሚችልም አይታወቅም::

የመረጃና ደህንነቱ ተቋም ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት አንድ መፍትሄ ብቻ አለው:: ይህም ኮንቴይነሩ ያለ ሌተር ኦፍ ክሬዲት (letter of credit) ወደ ኢትዮጵያ የሚገባበት ህጋዊ መንገድ ካለ መፈለግ ነው::

የመረጃና ደህንነት ተቋሙ አመራሮች የግርዶሽ መርህን በጥብቅ ባከበረ መንገድ ይህንን ፈተና ለመሻገር ከጉምሩክ ኮሚሽን ከፍተኛ አመራሮች ጋር ለመፍትሄ ተቀመጡ:: መፍትሄው ህግን ሳይጥሱ፣ ምስጢርም ሳያባክኑ ኮንቴይነሩ የጉምሩክ ኬላዎችን

እንዲሻገር የሚያስችል መሆን አለበት:: ከብዙ ምክክር በኋላ አንድ የህግ መሻገሪያ አሰራር ተገኘ። ኮንቴይነሩ ያለ ሌተር ኦፍ ክሬዲት (letter of credit) የጉምሩክ ኬላዎችን ሊያልፍ የሚችለው ምርቱ ለሙከራ ገበያ ከውጭ የሚመጣ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ስርዓት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ከሆነ ብቻ ነው። ይህ ፍቃድ ከጉምሩክ ኮሚሽን የሚገኝ በመሆኑ በኮሚሽኑ አመራሮች እገዛ አስመጭው ድርጅት ኮንቴይነሩን ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ የሚያስችለውን ፍቃድ አገኘ።



የመጀመሪያው ኮንቴይነር ከጅቡቲ ዱራሌ ኮንቴይነር ተርሚናል ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ

ጥር 12 ቀን 2012 ዓ.ም ኮንቴይነሩ አስፈላጊውን ሁሉ መስፈርት አሟልቶ ከጅቡቲ ዱራሌ ኮንቴይነር ተርሚናል ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመረ:: ኮንቴይነሩ ከጅቡቲ ከወጣ በኋላ ሁለት የጉዞ ሰነዶች የሚያስፈልጉት ሲሆን፤ የመጀመሪያው ከእዚያ እስኪወጣ ያገለግላል ሁለተኛው ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ እስከ አዲስ አበባ በየኬላው ለሚገኙ የጉምሩክ ኮሚሽን ጣቢያዎች የሚቀርብ ይሆናል። ይህ ሁሉ ከተሟላ በኋላ ኮንቴይነሩ ወደ አዲስ አበባ መጓዝ ሲጀምር እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ባስመጪው በኩል ፎቶ እየተነሳና ለባለቤቶቹ እየተላከላቸው ሂደቱን እንዲከታተሉና እምነት እንዲያድርባቸው ተደርጓል።

## የተቆለፈው ምስጢር ሲገለጽ

ኮንቴይነሩ ከጅቡቲ ዱራሌ ኮንቴይነር ተርሚናል ጀምሮ እስከ ጋላፊ የጉምሩክ ፍተሻ ጣቢያ ድረስ ያለ ምንም መሰናክል ተጓዘ። ጋላፊ በደረሰ ጊዜ ግን በጨረር መመርመሪያ መሳሪያ (x-ray) ማሽን ያልፍ ዘንድ ግድ ሆነ። ማሽኑ ደግሞ በኮንቴይነሩ የተቆለፈውን ምስጢር ይገልጻል:: ይህም ኦፕሬሽኑን ለመሩት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ሰዎች ጥርጣሬያቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲሆን፤ ላኪዎቹና ተቀባዮቻቸው ብቻ የሚያውቁትን ምስጢርም ይፋ ስለሚያደርግ በጉጉትና በስጋት ይጠበቃል። ውጤቱ በጨረር መፈተሻው ተገለፀ፤ ኮንቴይነሩም ምን እንደያዘ ታወቀ።




የመረጃ ኪነሙያን በተከተለ አካሄድ በጥብቅ ክትትልና ጠንካራ እጀባ አንዱን ኮንቴይነር በእጁ ያስገባው የመረጃና ደህንነቱ ተቋም ኮንቴይነሩን በእጁ የማስገባቱን ያህል ምስጢሩም ከእጁ እንዲወጣ አይፈልግም:: በመሆኑም የተቋሙ አመራሮች ከጉምሩክ ኮሚሽን አቻዎቻቸው ጋር በመነጋገር ቀድመው በነደፉት ስልት መሰረት የጨረር ምርመራው በተመረጠ ሰው እንዲከናወን ተደርጎ ምስጢሩ እንዳይወጣ ሆኖ ኮንቴይነሩ የያዘውን ይዞ የጉምሩክ ፍተሻ ጣቢያዎችን እንዲሻገር ተደረገ:: ኮንቴይነሩ ውስጡ ባለው እቃ ምክንያት በጉምሩክ ኮሚሽን ቢያዝ ላኪዎቹ መዳረሻ አገር ያልተፃፈበትን ቀሪውን ኮንቴይነር አይልኩም:: ስለዚህ የመረጃና ደህንነቱ ተቋም የመጀመሪያውን ኮንቴይነር የጋላፊን የጉምሩክ ፍተሻ ጣቢያ በረቀቀ መንገድ እንዲያልፍ አደረገ::

**ጥር 15 ቀን 2012 ዓ.ም** ከጅቡቲ ጀምሮ በመረጃና ደህንነት ሰዎች ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሲደረግበት የነበረው ኮንቴይነር ከአዲስ አበባ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ላይ ደረሰ:: ማረፊያና ማራገፊያውም የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በሽፋን የከፈተው የአስመጪው ድርጅት መጋዘን ውስጥ ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን፤ ኮንቴይነሩ ያለ ምንም ችግር የሚፈለገው ስፍራ መድረሱን የሚያረጋግጡ የፎቶ ማስረጃዎች ባህር ማዶ ለሚገኙት ድርጅቶች ተልኳል:: መጋዘን በገባ ጊዜም የኮንቴይነሩን ቁጥሮች ስለሚያውቁ በማሳየት እምነት እንዲጥሉ ተደርጓል::

ወዲያ በላኪዎቹ አመኔታን ያተረፈው አስመጭ ድርጅት፤ ወዲህ ደግሞ በአገርና በህዝብ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎበታልና ኮንቴይነሩ ተፈትሾ የያዘው ምስጢር እንዲገለጽ ግድ የሚልበት ወቅት ላይ ተደረሰ:: በመጀመሪያው ኮንቴይነር ውስጥ ከተገኙ 333 ካርቶኖች መካከል አንድ መቶ አስሩ ፀጉር ማድረቂያ ፣ምግብ ማብሰያ አነስተኛ ኦቭን ፣ውሃ ማሞቂያ እና ሌሎች የኤሌክትሪክ እቃዎች ማጽጃ መሣሪያዎች ይዘው ተገኙ:: ሌሎቹ 223 ልሙጥ ካርቶኖች ግን በአንዱ ካርቶን ላይ አራት ከመጉደሉ በቀር እያንዳንዳቸው 36 ሽጉጦችን መያዛቸው ተረጋገጠ::

# ብስለት የወለደው ውሳኔ

የመጀመሪያውን ኮንቴይነር በእጅ የማስገባቱ ተልእኮ በስኬት ተጠናቀቀ:: ሁለተኛውን ኮንቴይነር በተመሳሳይ መልኩ ከጅቡቲ አንስቶ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ንግግር በተጀመረበት ወቅት ግን ‹‹በመጀመሪያው ኮንቴይነር ውስጥ ያለውን ንብረት ኢትዮጵያ ላሉ ተቀባዮች አስረክቡ፤ ይህ ሳይሆን ሁለተኛውን ኮንቴይነር ማንቀሳቀስ አይቻልም›› የሚል ትዕዛዝ ከላኪዎቹ ተሰጠ::

አሁን ሁለት መጥፎ አማራጮች ከፊት ተደቀኑ:: የመጀመሪያው ዜጎች እርስ በእርስ እንዲተላለቁ የገባውን የጦር መሣሪያ ለተቀባዮች ማስረከብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በእጅ የገባውን ጦር መሣሪያ አምክኖ ጅቡቲ ወደብ ያለውንና መዳረሻ ስፍራው ያልተፃፈበትን ኮንቴይነር ማጣት ይሆናል:: የመጀመሪያውን ኮንቴይነር በእጁ ባስገባው ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በኩል ሁለቱም አማራጮች ተቀባይነት አላገኙም::

ዘመቻውን የሚመሩት የአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ዳይሬክተር ጀነራል እና ምክትላቸው ‹‹በመጀመሪያው ኮንቴይነር ውስጥ የተገኘውን ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ለተቀባዮች መስጠት በጭራሽ አይሞከርም›› የሚል አቋም ያዙ:: ሁለተኛው ኮንቴይነር ባለበት ቦታ ጅቡቲ መተውም በውስጡ ያለውን የጦር


ህገ ወጥ የጦር መሣሪያው የተራገፋበት መጋዘን

መሣሪያ አይነትና ብዛት ካለማወቅ ባሻገር፤ በሌላ አማራጭ ወደ አገሪቱ እንዲገባ እድል እስከ መስጠት ኪሳራ እና ጉዳት አለው:: ከሁሉም በላይ ግን ሁለተኛውን ኮንቴይነር ማጣት የህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ሰንሰለት የመበጣጠስ ዘመቻን ጎዶሎ ያደርገዋል:: ስለዚህ ሶስተኛና የተሻለ አማራጭ ያስፈልጋል፤ ይህም ሶስተኛ አማራጭ የአምዕሮ ብስለት፣ የስለላ ጥበብና በጦር መሣሪያ ዝውውር የካበተ ልምድ ያላቸውን ድርጅቶች የማሳመን አዕምሯዊ ልዕልና ይጠይቃል::




> . . . ስለዚህ ሶስተኛና የተሻለ አማራጭ ያስፈልጋል፣ ይህም ሶስተኛ አማራጭ የአምዕሮ ብስለት፣ የስለላ ጥበብና በጦር መሣሪያ ዝውውር የካበተ ልምድ ያላቸውን ድርጅቶች የማሳመን አዕምሯዊ ልዕልና ይጠይቃል

በኮንቴይነሮቹ ተጭነው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የተላኩትን ሁሉንም ህገ ወጥ የጦር መሣሪያዎች በእጅ የማስገባት እንዲሁም የአገር ውስጥ ተቀባዮችንም በቁጥጥር ስር እንዲውሉ አስፈላጊውን መረጃ የመሰብሰብ ዘመቻ የከፈተው የመረጃና ደህንነቱ ተቋም ተልዕኮውን ለማሳካት በመጀመሪያው ኮንቴይነር ውስጥ የመጣውን እቃ ለተቀባዮቹ ማስረከብ እንደማይቻል ለላኪዎቹ አሳማኝ ሀሳቦችና ምክንያቶችን ማቅረብ የተሻለ አማራጭ ነው ብሎ ነበር የወሰነው፡፡

ተቋሙ ባስመጪነት ሽፋን በከፈተው እና የመጀመሪያውን ኮንቴይነር ባስገባው ድርጅት በኩል ለላኪዎቹ የጥር ወር አጋማሽ የጥምቀት በዓል የሚከበርበት በመሆኑ በመላ አገሪቱ ጥብቅ ፍተሻ እንደሚካሄድና በዚህ ወቅት የጦር መሣሪያ በአገር ውስጥ ማዘዋወር የመያዝ እድልን ስለሚያሰፋ የማስረከቢያ ጊዜው ቢራዘም የሚል ማግባቢያ አማራጭ አቀረበ፡፡ አስመጪው የመጀመሪያው ኮንቴይነር ከጅቡቲ ወደብ ተነስቶ ኢትዮጵያ የገባበት የመጓጓዣ፣ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ በድምሩ 20 ሺ ዶላር ላኪዎቹ ሳይከፍሉት እቃውን ለተቀባዮቹ ማስረከብ እንደማይችልም በመግለፅ፣ ሁለቱንም ኮንቴይነሮች ወደ ኢትዮጵያ አስገብቶ እቃውን ማስረከብና ስራውን ማጠናቀቅ ይሻላል የሚል ሀሳብ ሰነዘረ፡፡

የኮንቴይነሮቹ ላኪዎች ከተወሰነ ማቅማማት በኋላ በሃሳቡ ተስማሙ፡፡ የመዳረሻ ስፍራ ፣የእቃ መዘርዝርና የክብደት መጠኑ ላልተገለጠለት ሁለተኛው ኮንቴይነርም አስፈላጊውን መረጃ አሟልተው በመላክ ከጅቡቲ

ወደ ኢትዮጵያ እንዲንቀሳቀስ ፈቀዱ፡፡ ለዚህ አላማ ሲባል በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የተቋቋመው አስመጪ ድርጅት ሁለተኛውንም ኮንቴይነር በእጁ አስገባ፡፡ በጥብቅ ክትትል፣ የቅርብ እጀባና ቁጥጥር ከጅቡቲ ዱራሌ ኮንቴይነር ተርሚናል አዲስ አበባ እንዲደርስም አደረገ፡፡

> “501 ካርቶኖች ምንም አይነት ፅሁፍ የሌለባቸውና የንግድ ምልክት ያልተለጠፈባቸው ሲሆኑ፤ በውስጣቸው 18 ሺ 32 ሽጉጥ ይዘዋል”

ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ሁለተኛው ኮንቴይነር ባስመጪው ድርጅት መጋዘን ውስጥ ደርሷል፡፡ አሁን ሁለቱ ኮንቴይነሮች ምን እንደያዙ በአይነትም በመጠንም ታውቋል፡፡ አጠቃላይ በሁለቱ ኮንቴይነሮች ውስጥ የተጫነው ካርቶን ብዛት 730 ነው፡፡ 501 ካርቶኖች ምንም አይነት ፅሁፍ የሌለባቸውና የንግድ ምልክት ያልተለጠፈባቸው ሲሆኑ፤ በውስጣቸው 18 ሺ 32 ሽጉጥ ይዘዋል፡፡ በ229 ካርቶኖች ውስጥ ለሽፋንነት የተዘጋጁ የተለያዩ ቁሶች ታሽገው ነበር፡፡







ሁለተኛው ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ የጫነ ተሽከርካሪ

## የመጨረሻው መጀመሪያ፤ የመጨረሻው መጨረሻ

አሁን ሌላኛው ትልቅ ተልዕኮ ከፊት ተደቅኗል፡፡ የሁለተኛው ምዕራፍ ኦፕሬሽን መጀመሪያ ሰአት ነው፡፡፡ ለጦር መሣሪያ ተቀባዮቹ የመጨረሻው መጀመሪያ፤ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ደግሞ የዘመቻው የመጨረሻው መጨረሻ፡፡ የገባውን የጦር መሣሪያ ተቀባዮች ማወቅ፤ መለየት፤ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያውን እንዲረከቡ ግንኙነት መፍጠር፤ ለመረከብ ሲመጡም ተጠርጣሪዎች በህግ ቁጥጥር ስር የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ በቁጥጥር ስር ለሚያውሏቸው የጸጥታ አካላት የተሟላና ትክክለኛ መረጃና ማስረጃ በመስጠት እንዲያዙ ማድረግ፤ ከጦር መሣሪያው ዝውውር ጀርባ ያሉትን ግለሰቦች በዝርዝር በመለየት አድኖ በማስያዝ መረቡን መበጣጠስ …

የካቲት 02 ቀን 2012 ዓ.ም ኮንቴይነሮቹን ከጅቡቲ ያስመጣው ለሽፋን የተቋቋመው ድርጅት ከላኪዎቹ ጋር ንግግሩን ቀጥሏል፡፡ አስመጪው ሁለቱን ኮንቴይነሮች ከጅቡቲ ያጓጓዘበት፤ መጋዘን የተከራየበትና ቀረጥ የከፈለበት ወጪ እንዲሸፈንለት አሜሪካን አገር ለሚገኘው ለላኪው ሊበርቲ ሺፒንግ ኤንድ ሎጅስቲክስ ድርጅት በኢሜይል ጠይቋል፡፡ ላኪው ድርጅት በኢሜይል መልስ ሰጠ፡፡ የተጠየቀውን 20 ሺ ዶላር ለመላክ ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ፤ የአስመጪው ድርጅት የባንክ ቁጥር እንዲሁም የወኪሉን ሙሉ አድራሻ እንደሚፈልግ መልስ ሰጠ፡፡ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ይህን ጉዳይ የሚከታተል ሌላ ሰው የአስመጪው ድርጅት ወኪል አድርጎ አዘጋጀ፡፡





ከብዙ የኢሜይል ልውውጥ በኋላ የኮንቴይነሩ ላኪዎች አስመጪው የጠየቀውን 20 ሺ ዶላር እቃውን ከሚረከቡት ኢትዮጵያውያን መቀበል እንደሚችል ገለጹ:: ‹‹አንድ ሰው ይደውልልሃል ከእርሱ ጋር ተነጋገር›› በማለት ለአስመጪው ድርጅት ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ ለሚንቀሳቀሰው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አባል አሳወቁ::

የካቲት 7 ቀን 2012 ዓ.ም በጦር መሣሪያው ተቀባዮችና የጦር መሣሪያውን ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ባስመጣው ድርጅት መካከል የመጀመሪያው የስልክ ግንኙነት ተደረገ:: በአስመጪው ድርጅት ጉዳይ አስፈፃሚነት ሽፋን የሚንቀሳቀሰው የመረጃ ኦፊሰሩ አህመድ ከሚባል ሰው ስልክ ተደወለለት:: ለመገናኘትም ተቀጣጠሩ፤ አዲስ አበባ ቦሌ አካባቢ ሶስት ሰዎች ከኦፊሰሩ ጋር ተገናኙ:: የጦር መሣሪያውን ከተራገፈበት መጋዘን አውጥቶ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ማሰራጨት ስለሚቻልበት ጊዜ እና ሁኔታ ተነጋገሩ:: የተጠየቀውንም 20 ሺ ዶላር ሶስቱ ሰዎች በኢትዮጵያ ብር ለመክፈል ተስማሙ:: በሽፋን የሚንቀሳቀሰው የመረጃ ኦፊሰርም ገንዘቡ ከተከፈለው የወከለው አስመጪ ድርጅት የሁለቱን ኮንቴይነሮች እቃ ለማስረከብ ዝግጁ መሆኑን አሳውቆ የመጀመሪያው የጦር መሣሪያ ተረካቢዎችና የመረጃ ኦፊሰሩ ግንኙነት በዚህ መልኩ ተደመደመ::

ከዚህ ወቅት ጀምሮ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ሶስት አመራሮች ብቻ የሚታወቀውን ኦፕሬሽን ሌሎች ሰዎች እንዲቀላቀሉት ተወሰነ፡፡ ይህ የተወሰነው የህገ ወጥ መሣሪያው ተቀባይ ኢትዮጵያውያንን ለመከታተል ተጨማሪ የሰው ሃይልና የቴክኖሎጂ እገዛ በማስፈለጉ ነው፡፡ በመሆኑም የተቋሙ የሰብዓዊ እና ቴክኒካዊ ክትትል ክፍሎች ኃላፊዎች አባሎቻቸውን ለልዩ የክትትል ዘመቻ እንዲያዘጋጁ ተደርጎ በሶስቱ ሰዎች ላይ ክትትል ተጀመረ፡፡ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትም ሶስቱን ተጠርጣሪዎች በሰውና በቴክኖሎጂ እገዛ ተከታትሎ መኖሪያ አድራሻቸውን፣ የኋላ ታሪካቸውንና የተሰማሩበትን የስራ መስክ ደረሰበት፡፡ አሁን የሶስቱ ሰዎች እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በአገልግሎቱ እይታ ውስጥ ነው፡፡

**የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም**
በቀጠሮው መሰረት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኦፊሰሩ አዲስ አበባ ስታድየም ተገኘ፡፡ የጦር መሣሪያው ተቀባዮችም አራት መቶ ሺ ብር በጥሬ ገንዘብ ይዘው በመምጣት ክፍያ ፈፀሙ፡፡

የጦር መሣሪያው ተረካቢዎች በዕለቱ ምሽት ላይ 50 ካርቶን እንጭናለን የሚል አቋም ያዙ፡፡ የመረጃና ደህንነቱ ተቋም ግን የጦር መሣሪያው በዚህ ፍጥነት ከመጋዘን እንዲንቀሳቀስ አልፈለገም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ጥቂት ተጨማሪ ቀን ቢገኝ በክትትል ስር የወደቁትን ሶስት ሰዎች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ በማጥናት አብረዋቸው የሚሰሩ ሌሎች ሰዎች ሊደረስባቸው ይችላል የሚል ፍላጎት ነው፡፡ የህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሩን አጠቃላይ ትስስር እንዲሁም አንዱ ከአንዱ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለውን ግንኙነት ለማወቅ ጊዜ መግዛት ወሳኝ ነው የሚልም መነሻ አለው፡፡ ለዚህም ሲባል እሁድ የትራፊክ እንቅስቃሴ የሚቀንስበት ቀን ስለሆነ፣ ፍተሻ ስለማይበዛና የሰው ትኩረትም ስለማይስብ ተመራጭ መሆኑን ለማሳመን የተደረገው ሙከራ ተሳክቶ ቀን ተቆረጠ፡፡

**እሁድ የካቲት 15 ቀን 2012 ዓ.ም፤**
ይህቺ ቀን በሁለቱ ኮንቴይነሮች ከመጣው 501 ካርቶን ሽጉጥ መካከል የመጀመሪያውን 50 ካርቶን ከመጋዘን አውጥቶ ለማስራጨት የተሻለች ሆና ተመረጠች፡፡ 50 ካርቶን ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ፤ ለህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ተቀባዮቹ የመጨረሻው መጀመሪያ፣ ለመረጃና ደህንነት መሥሪያ ቤቱ ደግሞ የመጨረሻው መጨረሻ፡፡ ለተቀባዮቹ በ50 ካርቶን የተጀመረው እስከ 501 ካርቶን እንዲቀጥል፤ ለመረጃና ደህንነት ሰዎች ደግሞ 50 ካርቶን ሽጉጥ ከተቀባዮች ዘንድ ሳይደርስ ሁሉንም በእጅ ለማስገባት - ግብግቡ ከዚህ ይጀምራል፡፡

> 50 ካርቶን ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ፤ ለህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ተቀባዮቹ የመጨረሻው መጀመሪያ፣ ለመረጃና ደህንነት መሥሪያ ቤቱ ደግሞ የመጨረሻው መጨረሻ:: ለተቀባዮቹ በ50 ካርቶን የተጀመረው እስከ 501 ካርቶን እንዲቀጥል፤ ለመረጃና ደህንነት ሰዎች ደግሞ 50 ካርቶን ሽጉጥ ከተቀባዮች ዘንድ ሳይደርስ ሁሉንም በእጅ ለማስገባት - ግብግቡ ከዚህ ይጀምራል

በዕለቱ የጦር መሣሪያው ተቀባዮች የተለያዩ ቡድኖችን በሶስት ስፍራዎች አሰማርተዋል፡፡ 50 ካርቶን የጦር መሣሪያ ለመረከብም አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቀዋል:: በሌላ በኩል የፌደራል፣የአፋር የአማራ፣የኦሮሚያና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አመራሮች ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አመራሮች ጋር ተቀናጅተው ባሳለፉት ውሳኔ መሰረት ተቀባዮች ባሉበት ቦታ ሁሉ የተዘጋጀ የፀጥታ ኃይል በተጠንቀቅ ቆሟል:: ተጠርጣሪዎቹን መያዣና የፍተሻ ትዕዛዝም ከፍርድ ቤት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡





ሶስት ሰዎች የያዘ አንድ ቡድን በአንድ የቤት መኪና ውስጥ ሆኖ አዲስ አበባ ሃያ ሁለት ድንበሯ ሆስፒታል አካባቢ ቆሟል፡፡ በሁለት የተከፈለ ቡድን ሁለት አቅጣጫ ይዞ ከዚህኛው ቡድን አንፃር በተጠንቀቅ ተሰልፏል:: አንድ ቢጫ ሲኖትራክ ወደ ገላን መስመር እያመራ ነው:: ይህንን ሲኖትራክ ወደሚፈለግበት ቦታ የምትመራው የቤት መኪና ከፊት መቅደም ጀመረች:: ሁለት አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ይህንን ሲኖትራክ በቅርብ ርቀት ከኋላ ይከታተላሉ፡፡

50 ካርቶን ለመውሰድ አስበው የመጡት የህገ ወጥ ጦር መሣሪያው አዘዋዋሪዎች ስልክ ደውለው ተጨማሪ 36 ካርቶን ጠይቀው ከጫኑ በኋላ በ86 ካርቶን 3 ሺ 96 ቱርክ ሰራሽ ሽጉጦችን መዳረሻው ባልተነገረው ሲኖትራክ ይዘው ከመጋዘኑ ወጡ:: የመረጃና ደህንነት መሥሪያ ቤቱ አባል ከባለቤቶቹ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተሽከርካሪውን ይመራል:: ክትትሎችም ክትትላቸውን ቀጥለዋል::

ተሽከርካሪው ከገላን ወደ ቃሊቲ ጉዞ ጀመረ፡፡ ቃሊቲ ውሃ ልማት አካባቢ የጦር መሣሪያ የጫነው ሲኖትራክ የመጨረሻ መዳረሻ ሆኖ አሽከርካሪው በታዘዘው ቦታ ቆመ:: የህገ ወጥ መሣሪያውን መጫን ያረጋገጡት ተቀባዮቹ ሲኖትራኩ እንዲቆም ካዘዙ በኋላ ከነበሩበት ሃያ ሁለት አካባቢ ተንቀሳቀሱ፡፡ ሶስቱን ግለሰቦች

“50 ካርቶን ለመውሰድ አስበው የመጡት የህገ ወጥ ጦር መሣሪያው አዘዋዋሪዎች ስልክ ደውለው ተጨማሪ 36 ካርቶን ጠይቀው ከጫኑ በኋላ በ86 ካርቶን 3 ሺ 96 ቱርክ ሰራሽ ሽጉጦችን መዳረሻው ባልተነገረው ሲኖትራክ ይዘው ከመጋዘኑ ወጡ”



86 ካርቶን ቱርክ ሰራሽ ሽጉጦች የጫነው ተሽከርካሪ

የጫነው የቤት መኪና በሰውና በካሜራ ስውር ክትትል ስር ነው:: በዚህ በክትትል ስር ካለው ሲግናል አካባቢ ወረደ:: ይህ ሰው ከቱርክ የተላከውን የጦር መሣሪያ በኢትዮጵያ ተቀብሎ የማሰራጨት ስራውን የሚመራው መሀመድ ጀማል ነው:: መሀመድ ከመኪናው ከወረደ በኋላ በቅርብ ርቀት ሲከታተሉት በነበሩ የፀጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ስር ዋለ::

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ኮንቴይነሮቹን የጫኑት ተሽከርካሪዎች ከጅቡቲ ወደብ ከወጡበት ደቂቃ ጀምሮ እቃውን እስካራገፉበት፤ የተራገፈው እቃ ከመጋዘን ወጥቶ ወደሚፈለገው ቦታ ሲጓጓዝም እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ክትትል ያደርግበት ነበር:: የጦር መሣሪያውን ያስጫኑት፣ ለመቀበል የተዘጋጁትና ገንዘቡን የከፈሉት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን በእጁ አስገብቷል::

# እነማን በቁጥጥር ስር ዋሉ?

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ባካሄደው ውጤታማ ኦፕሬሽንም የህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሩን መረብ መበጣጠስ ከመቻሉም ባሻገር፤ በሰጠው የተጣራ መረጃ በአዲስ አበባ ከተማ እንዲሁም በአማራና አፋር ክልሎች 24 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ሁለቱን ኮንቴይነር ከቱርክ ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ሰባት የውጭ አገራት ዜጎችና 4 የውጭ አገራት ድርጅቶች መሳተፋቸው ታውቋል፡፡

ከውጭ አገር ተጠርጣሪዎች አንዱና ዋናው ‹‹አቡልእዝ›› በሚል ቅፅል ስም የሚታወቀው አል ሶፊያን የተባለ ግለሰብ መቀመጫውን አሜሪካ ያደረገው ሊብርቲ ሺፒንግ ኤንድ ሎጀስቲክስ ኃላፊ ነው፡፡ ከቀሪዎቹ ስድስት ተጠርጣሪ የውጭ አገር ዜጎች መካከል ሁለቱ ሱዳናዊያን መሆናቸው ተደርሶበታል፡፡

ተጠርጣሪ የውጭ አገር ዜጎችን ከመያዝ አንፃርም ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከሱዳን አቻው ጋር ባደረገው ትብብር ሁለት ሱዳናዊያን ተጠርጣሪዎች እዛው ሱዳን ተይዘዋል፡፡ የቱርክ፣አሜሪካ ፣ሊቢያና ጅቡቲ የመረጃ ተቋማትም ከኢትዮጵያ አቻቸው የደረሳቸውን መረጃ ይዘው በህገ ወጥ መሣሪያ ዝውውሩ የተጠረጠሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ምስጢራዊ ክትትላቸውን ጀምረዋል፡፡




በአገር ውስጥ ከተለያዩ አካባቢዎች በቁጥጥር ስር ከዋሉት ተጠርጣሪዎች የተወሰኑት፤



በጦር መሳሪያ ዝውውሩ የተሳተፉ የተለያዩ አገራት ዜጎች፤

# ከጦር መሣሪያ ዝውውሩ ጀርባ ያደፈጠው ድብቅ አላማ

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አመራሮችና ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃትና ብልሃት ከተቋማዊ አቅም ጋር የታየበት ኦፕሬሽን አገርን ከጉዳት፤ ህዝብን ከእልቂት ታድጓል፡፡ በቁጥጥር ስር የዋለው 18 ሺ 32 ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ አገር ውስጥ ቢሰራጭ ሊያደርስ የሚችለውን አስከፊ አደጋ በግምት ብቻ መረዳት ይቻላል፡፡ በገንዘብ ደረጃ ከግማሽ ቢልዮን ብር በላይ ከፈሰሰበት የጦር መሣሪያ ዝውውር ጀርባ ያለው ሰንሰለት ደግሞ ከተለመደው ተመሳሳይ ወንጀል የተለየ ፖለቲካዊ ግብና ሴራ ያዘለ መሆኑን ጥርጣሬ የሚያጭሩ ጉዳዮች አሉ፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ፍቃዱ ፀጋ፤ በአገሪቱ የጦር መሣሪያ ዝውውር መብዛቱ እንዲሁም የጦር መሣሪያው አይነትና የሚጓጓዝባቸው ክልሎች ሲታዩ ጉዳዩ በህገ ወጥ መንገድ የሚገኝ ገንዘብ ብቻ ከመሻት የዘለለ ፖለቲካዊ አላማ እንዳዘለ ጥርጣሬ ያጭራል የሚል አስተያየት ሰንዝረዋል፡፡

‹‹መሣሪያዎቹ የሚዘዋወሩት ለግጭት የሚዳረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ ተብሎ በሚታመንባቸው አካባቢዎች ነው፡፡ የፈሰሰበት ገንዘብና መጠኑ ሲታይ ኢትዮጵያዊያንን እርስ በእርስ በማጫረስ አገርን የማዳከም ፖለቲካዊ ሴራ አካል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን የሚያካሂዱት አካላት በአገር ውስጥ የጦር መሣሪያዎችን ስርጭት በየቦታው በማስፋት ማንነትንና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች እንዲባባሱ፤ አለመረጋጋቶች እንዲቀጥሉ የማድረግ ፖለቲካዊ አላማ አላቸው ብዬ አስባለሁ›› ብለዋል፡፡

## ህጉ ምን ይላል?

ዛሬ ላይ ጉዳዩ የመርማሪ ፖሊስ፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግና የአገሪቱ የሕግ ስርአት እጅ ላይ ወድቋል። አዲሱ የህገ ወጥ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅም ጠንከር ያሉ ቅጣቶችን የያዘ ነው። በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ዳይሬክተሩ አቶ ፍቃዱ እንደሚያብራሩት፤ በአዋጁ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ማዘዋወር ፣ማጓጓዝ ፣መሸጥና መደለል ከ8-20 አመትና ከሶስት መቶ ሺ እስከ አምስት መቶ ሺ ብር የሚደርስ ገንዘብ ያስቀጣል።

## እንደ ማጠቃለያ

አሜሪካ፣ ቱርክ፣ ሊቢያ፣ ሱዳን፣ ጅቡቲና ኢትዮጵያን ያካለለው ድንበር ተሻጋሪው የጥፋት ሰንሰለት በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተበጣጥሷል። ከጀርባው ብዙ ሴራና ብዙ ገንዘብ ቢኖርም፤ ትርፉም የደም ነዋይ መሆኑ ቢታወቅም አገርን በሚጠብቁ ብልሆችና ትጉሃን ከሽፏል።

ኦፕሬሽኑ ከኢንተለጀንስ ኪነሙያ አንፃር ሲመዘን ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከአነስተኛ ጥቆማ በመነሳት፤ ምስጢርን ለቀናት ሳይሆን ለወራት በመጠበቅ፤ በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከአገር ውጪም ኦፕሬሽን በማካሄድ ጉልህ ስኬት ማስመዝገቡን ያሳያል። ይህም በኢንተለጀንስ ዘርፉ ልህቀትን እያሳየ ሙያዊ ብቃቱንም እያጎለበተ መሄዱንና መረጃ በመሰብሰብና በማቅረብ ብቻ ሳይታጠር ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ኦፕሬሽኖችን ለመፈፀም የሚያስችል ቁመና እየፈጠረ፣ የላቀ ግዳጅን የመፈጸም አቅም እያዳበረ በመሄድ ላይ የሚገኝ ተቋም መሆኑንም በግልጽ ያመላከተ ሆኗል።

> “ድንበር ተሻጋሪው የጥፋት ሰንሰለት በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተበጣጥሷል። ከጀርባው ብዙ ሴራና ብዙ ገንዘብ ቢኖርም፤ ትርፉም የደም ነዋይ መሆኑ ቢታወቅም አገርን በሚጠብቁ ብልሆችና ትጉሃን ከሽፏል”

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በዚህ ኦፕሬሽን ሂደት ከህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሩ ባሻገር ህገ ወጥ የሰው አካል ዝውውር መኖሩን የሚያሳይ መረጃ አግኝቶ ለሱዳን እና አሜሪካ አቻዎቹ መረጃውን አጋርቷል። በዚህም በአገር ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ላይ የሚያንዣብቡ ስጋቶችን አስቀድሞ በመተንበይ ለማስቀረት ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን በትብብር ለመከላከል ያለውን ቁርጠኝነት አስመስክሯል።

# ግብረ መልስ

‹‹የደም ነዋይ›› የተሰኘው ዶክመንተሪ መጋቢት 3 ቀን 2012 ዓ.ም ምሽት በተመሳሳይ ሰዓት በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት፣ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን፣ በዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት፣ በአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ (አዲስ ቲቪ)፣ በኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (ኦ ቢ ኤን) እና በአማራ መገናኛ ብዙሃን ተላልፏል:: በተጠቀሱት መገናኛ ብዙሃን ድረገጾች፣ የዩቲዩብ ቻናሎችና ይፋዊ የፌስቡክ ገጾች የተሰበሰቡ ግብረ መልሶች እንደጠቆሙት ዶክመንተሪውን በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ተመልክተውታል:: ከፍተኛ ግብረ መልስም ተገኝቶበታል::

የማህበራዊ ሚድያ ግብረ መልሶች በተለያዩ መለኪያዎችና መስፈርቶች ተመዝነዋል:: በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እና በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቲቪ) ዩቲዩብ እና ፌስቡክ ገጾች ብቻ በድምሩ 442 ሺ 743 ተመልካቾች፣ 7 ሺ 587 መውደድ(Like) ፣1ሺ436 አስተያየቶች ተሰጥተዋል:: በአማካኝ ከ85 በመቶ በላይ ገንቢ አስተያየቶች መሆናቸው የተደረገው የግብረ መልስ ዳሰሳ ያመለክታል::

ዶክመንተሪው ከመደበኛ መገናኛ ብዙሃን ባሻገር የግብረ መልስ ዳሰሳው ባላካተታቸው የተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች መታየቱ ታሳቢ ሲደረግ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተመልካቾች ዘንድ መድረሱ ግልጽ ነው::

ዶክመንተሪውን መሠረት በማድረግ የተሰጡት አስተያየቶች የተቋሙ የረቀቀ ክትትልና ሙያዊ ክህሎት ሊደነቅ እንደሚገባ፤ለስኬቱ የአመራሩና የሠራተኛው ሚና ከፍተኛ ስለመሆኑ፤አገርና ህዝብን ከጥፋት ለመታገድ ተቋሙ ጥበብ የተሞላበት ስራ እንደሚያከናውን ይህም በህዝብ ዘንድ ኩራት እንደፈጠረ፣ ተቋሙ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ተላቆ እየሰራ ስለመሆኑና የተበላሸ ገጽታው እየተቀየረ ስለመምጣቱ የሚያትቱ ናቸው::

በሌላ በኩል ዶክመንተሪውን በተመለከተ በማህበራዊ ሚዲያ ከተሰጡት ግብረ መልሶች መካከል 15 በመቶ የሚሆኑት መታረም አለባቸው የሚሉ ከተቆርቋሪነት



የመነጩ አስተያየቶች የሚበዛባቸው ሲሆን፤ ከአቀራረብና ይዘት ጋር በተያያዘ ዶክመንተሪው ከግምት ውስጥ ቢያስገባቸው ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ እይታዎችና ጥቆማዎችም ተሰንዝረዋል፡፡

ዶክመንተሪ ፊልሙ በመገናኛ ብዙሃን ከተላለፈ በኋላ በሰፊው የመነጋገሪያ አጀንዳ ለመሆን በቅቷል፤ የኦፕሬሽኑ ስኬት የህብረተሰቡን ቀልብ መግዛት ችሏል፡፡ ከህብረተሰብ ጋር የሚያገናኝ ድልድይ መፍጠር ብሎም ጠብቆ ማዝለቅ ለመረጃ ተቋም ውጤታማነት እንደ መሠረት ድንጋይ የሚያገለግል በመሆኑ ዶክመንተሪው እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ለአገሪቱ የደህንነት ስጋት የሆነውን ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ለመግታት የላቀ የህብረተሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ ዘጋቢ ፊልም አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ለሚመለከታቸው አካላት ጥቆማ የመስጠት ተነሳሽነትን ያሳድጋል፡፡

**በማህበራዊ ሚድያ ከተሰጡት አስተያየቶች የተወሰኑት ለአብነት ቀርበዋል፤**

1. ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እና ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቲቪ) የፌስቡክ ገፅ የተገኙ አስተያየቶች

## Aziz Tesfatsion

- የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ግሩም የሆነ ስራ ሰርታችኋል በርቱ እናመሰግናችኋለን፡፡

## Getachew Wondim

- የደህንነት ተቋሙ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት የስልጣን ወንበር ለመጠበቅ ብቻ በጭካኔ ከመስራትና የገዛ ዜጎቹን በጨለማ እያሳደደ ከመቀጥቀጥና መሰወር ወጥቶ እንዲህ ሀገርንና ህዝብን ከመዓትና ከእልቂት የሚጠብቅ ስራ በትእግስት፣ በጥበብና በብቃት ሲሰራ ከማየት በላይ ለውጥ የለም፡፡ ክብርና ምስጋና ለደህንነት ተቋሙና ሰራተኞቹ፡ እናመሰግናለን፡፡

## Yeabsira Afomiya

- ክብርና ኩራት ለሀገራችን መረጃ እና ደህንነት ሰራተኞች በሙሉ፡፡


## Ephrem Gebrou Zeray

- እጅግ ጥበብ የተሞላበት ክትትል ነው የሚመሰገን ፕሮፌሽናል ስራ

## Zoe

- የሚደንቁ የደህንነት ደጀን ብዬአቸዋለሁ፡፡ የሀገር ሰላም ለማወክ የሚሮጡትን በብልሀት እግር በእግር ተከታትሎ ለህግ እንዲቀርቡ በማድረግ ሂደት ውስጥ ያሳዩት ብልሀት ብቃታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጀግኖች ናችሁ በርቱ !

## 2. ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቲቪ) ዩቲዩብ ገፅ የተገኙ አስተያየቶች



YouTube Search

EBC
487K subscribers
SUBSCRIBE

#ebc #etv
#EthiopianBroadcastingCorporation


159 Comments SORT BY

Add a public comment...

Melaku Betela 2 months ago
በደህንንት መስሪያ ቤቱ ብቃት ተገርሜያለሁ ከፈጣሪ በታች ሰላማችን በእጃችሁ ነው በርቱልን
18 REPLY

mehret Mekuria 2 months ago
በጣም የሚያኮራ የጀግንነት ስራ ነው የተሰራው ነገር ግን እንደነዚህ አይነት ወንጀለኞች የሚቀጡበት ቅጣት አሁንም ጠንካራ አይደለም ለሌላው መቀጣጫ በሚሆንበት መልኩ መሠራት አለበት ባይ ነኝ
12 REPLY

Sasa Sasa 2 months ago
Thank God.
You deserve 🎖 🏅🏅.
Above all my God protection always be with you



YouTube Search

Mulugeta Tadesse 2 months ago
Very wonderful job. Honestly, I proud of being Ethiopia. I will pay my deepest respect for this brilliant team of security. This act shows the nude fact of commitment will direct to the tower of success and prosperity.
11 REPLY

Mulugeta Gebre 2 months ago
ግብጽ እጇ እንዳለበት ግልጽ ነው
15 REPLY

RediT Kk 2 months ago
VERY #PROUD OF OUR NATIONAL SECURITY!!! 💚💛🖤 God Bless Ethiopia!
13 REPLY

david orsa 1 month ago
"Bravo" an Ethiopian intelligent!!! Thank you very much for what you have done for Ethiopia and Ethiopian!!! God bless and protect dear an Ethiopian intelligent officers as they carry on these kind of outstanding life saving job. Death for the internal and external enemies of Ethiopia!!
4 REPLY

Hanna 2 months ago
እንጀራና ውሃ ለሚያስፈልገው ህዝብ ያሚያልሙለት ጥይት ነው ይገርማል:: በጣም የሚያኮራ ስራ ነው የሰራችሁት:: እግዚአብሔር ይርዳችሁ ቀጥሉ::
5 REPLY

YouTube Search

samira daoudshifa 2 months ago
በጣም እምታኮሩ ናችሁ አደኘ ሕዝብ አተረፋችሁ ሁለተኛ የወር,ጋን ትራፊክ አዳናችሁ በርቱልን ራሳችሁም ጠብቁ እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ አሜን
3 REPLY

Seblewongle Shibeshi 2 months ago
ኢትዮጵያ ምቀኛዋ ብዙ ነው
ሕዝቤ አስተውል::
ድር ቢያብር አንበሳ ያስር::
በሁለት ወይም በሶስት የተሸረበ የተገመድ አይበጠስም ::...
Read more
3 REPLY

Engshe Eshetu 1 month ago
በጣም ጉሩም ኦፕሬሽን ነው በርቱ እንደዚህ ጎበዝ አትመስሉኝም ነበር
REPLY

yemi Esa 2 months ago
Good job well done so smart 🙏
3 REPLY

Gannet Youssef 1 month ago
የምገርም ጀግንነት እሰይ ወገኔቼ አዳናቹሁልን

YouTube Search

Seada Ahmed 1 month ago (edited)
Well done NISS🙏👌God bless Ethiopia 💚💛🖤
2 REPLY

janet tadese 1 month ago
ለመያዝ ከተፈለገ እንዲህ ይያዛል በጣም ደስ ይላል በርቱ
3 REPLY

Assefa Woldeselassie 2 months ago
ዋው! ንጹሃን የኢትዮጵያ ብርቅየ ልጆች ጀግኖች። እንዲህ የእናንተን ተግባር የሚቀጥሉ ታድያ ውለዱና አሳድጉ። ትልቅ ሥራ ነው። እነዚህ የቀንና የሌሊት ጅቦች እንዲህ አጥምዳችሁ በመያዛችሁ ኮራሁባችሁ። ገና ብዙ አድካሚና ወገብን ጠበቅ የሚያስደርግ ሥራ ይጠብቃችኋል። ግን ጀምራችሁታል ቀጥሉ, በርቱ!
የደህንነትና መረጃ ኮሚሽን እነዚህን ቀበሮች እንዲህ አጥምዳችሁ በመያዛችሁ ትልቅ ሥራ ሠርታችኋል።...
Read more
4 REPLY

tenagna Degafa 2 months ago
በጣም ሊመሰገኑ ይገባቸዋል
4 REPLY

zelalem mekuria 1 month ago
የደህንነት መስርያ ቤቱ የሰራው ሥራ እጅግ በጣም የሚመሰገንና ከምንም በላይ አድናቆትና ክብር ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው:: ብሄራዊ መረጃና ደህንነታችን የሰራው አኩሪ ተግባር በዚህ መልኩ ለሚዲያ መቅረቡ በቀጣይ ለሚሰራቸው መሰል ተግባሮች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድርበት ይመስለኛል:: የእኛ አንበሶች አደንቃችኋለሁ በርቱ ፈጣሪ ይርዳችሁ፡ እኛም ከጎናችሁ ነን!

# 3. ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዩቲዩብ ገፅ የተገኙ አስተያየቶች

YouTube Search

Fana Television
441K subscribers
SUBSCRIBE

የደም ነዋይ ዘጋቢ ፊልም #ፋና

SHOW MORE

YouTube Search

Yekolo Temari 2 months ago
ብሄራዊ መርጃና ደህንነት መሥርያ ቤታችን አሁን የሃገርንና የህዝብን ሥራና የተጣለበትን አደራ እንዲህ ነው መሥራትና ሃገርን መጠበቅ እኩሪ ተግባር
በርቱ እንኮራባችሁዋለን እስከመጨረሻው ተከታተሉት እንኮራባችሁዋለን አሁን ትክክለኛ ይህዝብ ደህንነት አካል መሆናችሁን አስመስክራችሁዋልና !!!!!
REPLY

Getachew Demissie 2 months ago
You did good job .
REPLY

Terrefe Berhanu 2 months ago
Great job
REPLY

endrisadane Adane 2 months ago
በጣም ጥሩ ውጤት ነው በርቱልን
REPLY

Tigista Asfaw 2 months ago
Great job
1 REPLY

YouTube Search

hoper of win 2 months ago
amaizing worke i wante to be member of etss
REPLY


Brook Bekele 2 months ago
we thank you very much for every thing that you have done i am so proud of you anbesoch
6 REPLY

Timkehet Teffera Mekonnen 2 months ago
አቤት ክፋቱ እና ሴራው ቀርቶብን ለጥሩ ነገር ብቻ ለፍተን በሆነ ኖሮ ዛሬ ኢትዮጵያ እና ምስኪኑ ሕዝቧ የት በደረሰ ነበረ። ለማንኛውም የመረጃና ድህንነትን ተቋም ታላቅ ሀግራዊ ተልዕኮ አድንቄአልሁ። እግዚአብሄር ይስጥልኝ ወገኖቼ።
1 REPLY

meskerem melese 2 months ago
Great!!! I Really Proud of You!!!
REPLY

نواف طس 2 months ago
ግሩም ክትትል!!!!
8 REPLY

Teddy Siyoum 2 months ago
Impressive keep it up!



YouTube Search


Sebli Magha 2 months ago
የብሄራዊ መረጃ ደህንነትን ሳላደንቅ ማለፍ ይከብደኛል በጣም አሪፍ ስራ ነው
10 REPLY

lisaf taddesse 2 months ago
እንዲህ አይነቶችን ሀገር ወዳድ ያብዛልን መንግስታችንም ሀገርን የማዳኑን ሀገር የመጠበቁን ጉዳይ ያጠናክረው
REPLY

Yekolo Temari 2 months ago
የጸጥታ ትቅዋማችንንም አንጠራጥረው የሃገር ደህንነት ከፍተኛ ሃላፊነት ስላለበት እንደቀድሞው ህዝብን ብማፈን ሳይሆን ሃገርንና ህዝብን ለመጠበቅ
ስለተሰማራ !!!!!
REPLY

Caterina Bettioni 2 months ago
Well done 👍 we are proud of your Organization you saved so many life's ✊👏👏👏
3 REPLY

FIRA'OL DEBEBE 2 months ago
35:00 ስሞቻቸው ምን ያሳያል???? 🤔
REPLY



YouTube Search

SEMIRA سميره 2 months ago
ደስ ሚል አቀራረብ ምርጥ ምሽን ገራሚ ውጤት አቦ አላህ ይጠብቃቹ ።
1 REPLY

feven araya 2 months ago
thank you for keeping us safe
REPLY

Son of the king 2 months ago
Great job and amazing operation, keep it long and work hard more
REPLY

Dani Mesa 3 weeks ago
በጣም ደስይላ አሪፍ ጀግንነት ነው ከአሁን በኋላ ያለውንም መዳህኒአለም ያግዛችሁ።
REPLY

tesfaye solomon 2 months ago
i proud of NISS it's great job keep continue
REPLY

Yekolo Temari 2 months ago (edited)
ይህንንም የምንለው የተያዙትን ግለሰቦች ጥብቅ ክትትልና መረጃ አገናዝባችሁ ማን ከበስተሁዋላው እንዳለ አብጠልጥላችሁ ለህዝብ ግልጽ እንድታደርጉ እናሳስባለን እንኮራባችሁውለን እናከብራችሁዋለን እናት የሞተች እንደሁ ባገር ይለቀሳል አባት የሞተ እንደሁ ባገር ይለቀሳል ሃገር የጠፋ እንደሁ ወዴት ይደረሳል ነውናነገሩ አደራ

## ተቋማዊ ራዕይ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት ጥቅሞችን ለመከላከል፣ ለመጠበቅና ለማሳደግ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የመረጃ ተቋም መሆን ነው፤

## ተቋማዊ ተልዕኮ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የደህንነት ስጋቶችና መልካም አጋጣሚዎች ላይ በጣም ተፈላጊና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ማቅረብ ነው፤

## ተቋማዊ ዕሴቶች

- ሀቀኝነት
- ዝግጁነት
- ልህቀት
- ምስጢራዊነት
- መደጋገፍ
- ተጠያቂነት

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አሸባሪዎች በአገራችን ላይ ጥቃት ከማድረሳቸው አስቀድሞ መረጃና ማስረጃ በማቅረብና በመተንተን አደጋውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የሰራው ስራ ውጤታማ ነው። በአገር ውስጥም ሆነ በጎረቤት አገሮች አካባቢ የተደራጁና የተቀናጁ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በቂ መረጃና ማስረጃ በማቅረብ ጉዳት ከመድረሱ አስቀድሞ በመመከት በኩልም አኩሪ ተግባር እየፈጸመ ይገኛል። በቅርቡ ድንበር ተሻጋሪ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ አዘዋዋሪዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ያካሄደው እጅግ የረቀቀ የመረጃ ብቃት የታየበት ኦፐሬሽን ለዚህ ማሳያ ይሆናል። የኦፐሬሽኑ ስኬት ተቋሙ ምርጥ የመረጃ ባለሙያዎችን ያፈራ መሆኑን አመልክቷል። ከለውጡ በኋላ ሌት ተቀን ለሕዝብና ለአገር የሚታትሩ አመራሮችም የጋራ ውጤት በመሆኑ በምክር ቤቱ እና በቋሚ ኮሚቴው ስም ማመስገን እወዳለሁ።

**አቶ ተስፋዬ ዳባ**

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የብሔራዊ ደህንነት ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረቀቀ፣ እየተወሳሰበና እየተጠናከረ የሚሄድ ነው። በዚህ ውስብስብ የስጋት ድባብ ውስጥ አሸንፎ ለመውጣት ጊዜው በሚጠብቀው ልክ እያደገ የሚሄድ የመረጃና ደህንነት ስራ ይጠይቃል። በዚህ ጽሁፍ የምናየውም ይህንን ነው። ተቋማዊ አቅም በትምህርትና በተሞክሮ እየዳበረ የሚሄድ ድምር አቅም ነው። ይህን ለማሳካት ደግሞ ስኬቶቻችንም ሆነ ውድቀቶቻችንን በሚገባ ሰንደን ማስቀመጥ ይገባል። ይህ ጽሁፍ ለብዙ ቀጣይ መማሪያ ሰነዶች መነሻ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ቴክኖሎጂ በፈጠረው አቅም ምክንያት በአሁኑ ወቅት ቡድኖች አንዳች ጥቃት ለመፈጸም በአንድ ቦታ መሰባሰብ ሳይጠበቅባቸው በመላው ዓለም እንደተበተኑ መከወን ይችላሉ። ይህን ለመግታት ሰፊ ዝግጅት፣ ጥብቅ ዲሲፕሊንና የላቀ ትጋት ይጠይቃል። ታሪኩ የሚያሳየንም ይህንኑ ነው።

**አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ**

የጠቅላይሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮች አማካሪ
ሚኒስትር ዴኤታ

ተልዕኮን በላቀ ሙያዊ ብቃት ለመወጣት የተሄደበት መንገድ የዜጋ ተኮር አመራር ነፀብራቅ ነው። በዚህ ኦፕሬሽን ቁርጠኝነት፣ ቀድሞ መገኘት፣ ፈጠራና የመፈፀም ብቃት ታይቷል። የዘመናዊ ኢንተለጀንስ መሰረቱ መንግስትን ማገልገል ሳይሆን፤ በተቋሙ የተልዕኮ አፈጻጸም እንደታየው አገርንና ዜጎችን ከአደጋ መታደግ ነው። ለዚህም አድናቆት ይገባችኋል! መልካም ስራ ነው! በዚሁ ቀጥሉ!

**ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሰላምና ደህንነት ጥናት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር